የሰ/መ/ቁ. 52595

ታህሳስ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ነገረ ፈጅ መና ህብስቱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ ሻሎም ተስፋዬ

2 ርግዓእት ገብረእየሱስ

3. ብርቱካን ገብረእየሱስ

4. ራዓዋ ገብረእየሱስ

(1-4) አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የክርክሩ መሠታዊ ጉዳይ አመልካች እንደስላሴ ከተማ ቀበሌ 02 ህንፃ ሠርቶ እንዲያስረክበው በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳች ለነበሩት አቶ አዲሱ አብርሀ በህንፃ ሥራ ውል ሠጥቷል፡፡ በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አዲስ አብርሀ የአንደኛ ተጠሪን ባለቤትና ስማቸው ከሁለተኛው ተራ ቁጥር እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር የተገለፀውን ተጠሪዎች ወላጅ አባት አቶ ገብረእየሱስ አባይን ቀጥሮ ሥራ በመሥራት ላይ እያሉ አቶ ገብረእየሱስ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በግንባታ ላይ ካለው ህንፃ ላይ ወድቀው በደረሰባቸው ጉዳት ወደ ሆስፒታል ከተወሰዱ በኋላ ነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች አመልካች በግንባታ ላይ የሚገኘው ጅምር ህንፃ ባለቤት በመሆናቸው አቶ አዲሱ አብርሀ የሟች የአቶ ገብረእየሱስ አባይ ቀጣሪ በመሆናቸው በሟች መሞት ምክንያት ለደረሰብን ጉዳት ብር 154,200 /አንድ መቶ ሀምሣ አራት ሺ ሁለት መቶ ብር/ እንዲከፍሉን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ሟች ህንፃውን ለመሥራት የተዋዋለው ሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ በመሆናቸውና ከህንፃው ወድቀው ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ በኋላፊነት የሚጠየቀው የሟች አሠሪ እንጅ እኔ አይደለሁም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ አመልካችና የሟች አሠሪ በአንድነትና በነጠላ

ለጉዳቱ ሀላፊ ናቸው በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አዲሱ አብርሀና አመልካች በአንድነትና በነጠላ ለተጠሪዎች /ከሳሾች/ ብር 36,000 /ሰላሣ ስድስት ሺ ብር/ የዳኝነትና ሌሎች ወጭዎችን በቁርጥ ፍርድ ቤቱ ወስኖ ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የህንፃው ባለቤት ከውል ውጭ በሀላፊነት ሊጠይቅ የሚቻለው ህንፃው ለሚያደርሰው ጉዳት ብቻ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2077 ተደንግጓል፡፡ ህንፃው በአሠራር ጉድለት ፈርሶ ወይም የህንፃው ክፍል የሆነ ነገር ወድቆ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ከላይ በተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ መሠረት ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ይኖርብናል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሟች የኮንትራክተሩ ሠራተኛ ናቸው፡፡ ሟች ሥራ እየሠሩ እያለ ከህንፃው ላይ ወድቀው ለደረሰባቸው ጉዳት ህንፃውን ለተቋራጭ ሠጥቶ እየሠራ ያለው አመልካች በኃላፊነት የሚጠይቅበት የህግ አግባብ ሣይኖር ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት አለባችሁ ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሟች የሞተው ከህንፃው ላይ ወድቆ ነው፡፡ ሟች የወደቀው ህንፃው የተሠራበት ቶንዲኖ ብረት በመታጠፉ ምክንያት ነው፡፡ አመልካች በውሣኔው መሠረት ድርሻውን ከፍሏል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በሟች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሟች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ለሞት የተዳረጉት የአመልካችን ህንፃ የሥራ ተቋራጭ ሆኖ የሚሠራው የሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ ሆነው ህንፃውን እየሰሩ እያሉ ከህንፃው ላይ ወድቀው ነው፡፡ የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ሟች ህንፃውን ከሚሰራው ኮንትራክተር ጋር በነበራቸው ውል መሠረት ህንፃውን ሲሰሩ ወድቀው ለደረሰባቸው የሞት አደጋ አመልካች ኃላፊ የሚሆነው በየትኛው የሕግ ድንጋጌ መሠረት እንደሆነ አልጠቀሱም በአመልካችና በሟች መካከል የውል ግንኙነት የሌለ በመሆኑ አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ የሚሆነው ከውል ውጭ በሚመጣ ኃላፊነት የሕግ ድንጋጌዎች አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚደነግጉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

አመልካች እየተሠራ ያለው ጅምር ህንፃ ባለቤት መሆኑ አልተካደም፡፡ የአንድ ህንፃ ወይም ቤት ባለቤት ከውል ውጭ ኃላፊ የሚሆንበት መሠረታዊ መርህ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ይዘት "የአንድ ህንፃ ባለሀብት ወይም ለይዞታ ሕንፃው ሊደርስ ይችላል ተብሎ ያልታሰበ ድንገተኛ ነገር ቢደርስም ይኸ ህንፃ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ ነው" የሚል ነው፡፡ ሟች በመገንባት ያለው ህንፃ በመፍረሱ ወይም የህንፃው አንድ ክፍል በመደርመሱ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው የሞት አደጋ ያጋጠማቸው ሰው አይደሉም፡፡ ሟችን የሞት አደጋ ያጋጠማቸው ህንፃውን የሚሠራው ኮንትራክተር ሠራተኛ ሆነው ህንፃውን በመሥራት ላይ እያሉ ከህንፃው ላይ

በመውደቃቸው ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ አይደለም፡፡

ሟች አመልካች የሚያሠራውን ህንፃ በውል የመሥራት ግዴታ ካለበት የሥራ ተቋራጭ ጋር ባላቸው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በሥራ ላይ እያሉ ወድቀው የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡ ይኸም በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ስለሚሰጡ ክፍያዎች በሚለው በምዕራፍ ሶስት ሥር የሚሸፈንና የሚተዳደር እንጅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሚወድቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በሟች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሀላፊ ስለሆነ ለተጠሪዎች ካሣ መክፈል አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልል የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ካሣ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ